# በተማሪ መብቶች አጠባበቅ (PPRA)
# ማሻሻያ ሥር እንደተደነገገው መብቶችን ሥለማስታወቅ

ይህ ማስታወቂያ ለወላጆች፣ ለልጅ አሳዳጊዎች እና ብቁ ለሆኑ (eligible) ተማሪዎች (ራሳቸውን ለቻሉ ልጆች ወይም እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ) የዳሰሳ ጥናት ከማከናወን ጋር፣ለንግድ ማስተዋወቂያ ዓላማ መረጃ ከመሰብሰብና መጠቀም ጋር እንዲሁም አንዳንድ አካላዊ ምርመራ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ስላላቸው መብቶች መረጃ ይሰጣል። እነዚህ መብቶች *በተማሪ መብቶች አጠባበቅ ማሻሻያ* (20 U.S.C. § 1232h; 34 CFR ክፍል 98) በግልፅ ተቀምጠዋል። በሕግና ደንብ እንደተቀመጠው የትምህርት ተቋዋማት እንደ የሞንጎመሪ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) የመሳሰሉት ለወላጆች እና ለልጆች አሳዳጊዎች(guardians) እንዲሁም ብቁ (eligible) ለሆኑ ተማሪዎች ስለመብቶቻቸው ማሳወቅ እንዳለባችው ይደነግጋል።

1. *ሥምምነት* ተማሪዎች ከዳሰሳ ጥናት ጋር በተያያዘ መረጃ እንዲሰጡ ከመጠየቃቸው በፊት ከሚከተሉት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጥበቃ የተደረገላቸው አካባቢዎች ("ጥበቃ የተደረገላቸው መረጃዎች ዳሰሳ ጥናት) ሲሆኑ፣ የዳሰሳ ጥናቱ በሙሉ ወይም በከፊል በዩ ኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ ኤዱኬሽን (U.S. Department of Education-USDE) የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወን ከሆነ
   - የተማሪው/ዋ/ወይም የተማሪው/ዋ/ወላጆች/አሳዳጊዎች የፖለቲካ እምነት ወይም ተዛምዶ (affiliations)፤
   - የተማሪው/ዋ/ወይም የተማሪው/ዋ/ቤተሰብ የአእምሮ ወይም የስነ ልቦና ችግሮች፤
   - የፍትወተ ስጋ ፀባይ ወይም አመለካከቶች፤
   - ህገወጥ፣ ማህበረሰቡን የሚፃረር፣እራስን የሚወነጅል፣ ወይም የሚያሳንስ ፀባይ፤
   - መልስ ሰጪዎች የቅርብ የቤተሰብ የዝምድና ግንኙነት ስላላቸው ሌሎች ሰዎች የሚተች ግምገማ፤
   - በህግ እውቅና ያላቸው ልዩ መብቶች እንደ ከህግ ባለሙያዎች ጋር፣ ሀኪሞች ጋር፣ ወይም መንፈሳዊ ሰባኪዎች ጋር ያሉ ግንኙነቶች፤
   - የተማሪውን/ዋን ወይም የተማሪው/ዋን ወላጆች/አሳዳጊዎች ሐይማኖታዊ ትግበራዎች፣ ቁርኝትነቶች ወይም እምነቶች፤
   - ለፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን ህግ ከሚጠይቀው በቀር ገቢ (Income)፤

2. *ማስታወቂያ መቀበል እና የመመርመር እድል ማንኛውም የሶስተኛ ወገን የዳሰሳ ጥናትን፣ጥበቃ የተደረገላቸው መረጃዎችን ዳሰሳ ጥናት፤ የተማሪዎች መረጃዎችን ለንግድ ማስተዋወቂያ ወይም ሽያጭ ዓላማ መሰብሰቢያ ዘዴን ወይም የተማሪዎችን የትምህርት ሥራዓተ ትምህርት* (ካሪኩለም) አካል ሆኖ በማስተማሪያ ቁሳቁስነት የሚያገለግልን፤

3. *ማስታወቂያ የመቀበል እና የተማሪን ያለመሳተፍ የመምረጥ እድል ማግኘትን*
   - **ከማንኛውም ሌላ ጥበቃ ከተደረገላቸው መረጃዎች ዳሰሳ ጥናት፤ የገንዘብ ምደባው (funding) ከምንም ይሁን ምን**
   - **ማንኛውም ያስቸኩዋይ ጊዜ ያልሆነ፣ ሙሉ አካላዊ ምርመራ (invasive physical exam) ወይም ትምህርት ለመከታተል በቅድመ ሁኔታነት አስፈላጊ ሆኖ በትምህርት ቤት ወይም በወኪሉ የሚከናወን እና የተማሪው/ዋን አስቸኩዋይ ጤንነት እና ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ያልሆኑ፤ ከሌድ (lead)፤ከመስማት (hearing) ወይም ከማየት (vision) ምርመራ ወይም ከማንኛውም የአካል ምርመራ ወይም በግዛቱ ህግ (state law) ከተፈቀዱት ወይም ከሚያስፈልጉት ምርመራዎች በስተቀር፤ እንዲሁም**
   - **ከተማሪዎች የተገኙ የግል መረጃዎችን የመሰብሰብ፤ ይፋ የማድረግ ወይም ለግብይት ወይም ሽያጭ ወይም መረጃዎችን በማንኛውም መልኩ ለሌሎች የማሰራጨት እንቅስቃሴዎች**

የሞንጎመሪ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) እነዚህን መብቶች በሚመለከት ፖሊሲዎች ቀርፆዋል። ተቀብሎዋል እንዲሁም ጥበቃ ከተደረገላቸው የዳሰሳ ጥናቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የተማሪዎችን የግል መረጃዎች ለመጠበቅ፤ የግል መረጃዎችን መሰብሰብን፣ ይፋ ማድረግን፣ እንዲሁም ለግብይት ወይም ሽያጭ ወይም ለሌሎች የማሰራጨት አላማን ክትትልና ቁጥጥርን አመቻችቱዋል። የሞንጎመሪ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) እነዚህን ፖሊሲዎች በአመት ቢያንስ አንድ ጊዜ በየአመቱ የትምህርት መጀመሪያ ወቅት እንዲሁም መሰረታዊ ለውጦች ከተደረጉ በኍዋላ ለወላጆች፤ ለልጅ አሳዳጊዎች እና ብቁ (eligible) ለሆኑ ተማሪዎች በቀጥታ ያሳውቃል።

የሞንጎመሪ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) በተጨማሪ<u>በቀጥታ</u>ለወላጆች፤ ለልጅ አሳዳጊዎች እና ብቁ (eligible) ለሆኑ ተማሪዎች በዩ.ኤስ ፖስታ ወይም ኢሜይል፣ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ በየአመቱ የትምህርት መጀመሪያ ወቅት፣ የሚከተሉትን እንቅስቃሴዎች ወይም ድርጊቶች የተለዩ ቀኖች ወይም ተቀራራቢ ቀኖችን በማሳወቅ ተማሪው/ዋ ላለመሳተፍ የመምረጥ እድል እንዲያገኝ ወይም እንድታገኝ ይሰጣል።

- የግል መረጃን መሰብሰብን፡ ይፋ ማድረግን፣ ወይም ለግብይት፣ ሽያጭ ወይም ሌላ ስርጭት መጠቀምን፤
- በዩ ኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ ኤዱኬሽን (U.S. Department of Education-USDE) በሙሉ ወይም በከፊል የገንዘብ ድጋፍ የማይከናወንን ማንኛውንም ጥበቃ የተደረገለትን መረጃ ዳሰሳ ጥናትን፤ እና
- ከላይ እንደተገለፀው ማንኛውም ያስቸኩዋይ ጊዜ ያልሆነ (nonemergency) ሙሉ አካላዊ ምርመራ (invasive physical exam)

መብቶቻችን ተጥሶብናል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች (guardians) እንዲሁም ብቁ (eligible) የሆኑ ተማሪዎች አቤቱታቸውን ለሚከተለው ማቅረብ ይችላሉ፡-

Family Policy Compliance Office (የቤተሰብ ፖሊሲ አስፈጻሚ/አስከባሪ ጽ/ቤት)
U.S. Department of Education (ዩ. ኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ ኤዱኬሽን)
400 Maryland Avenue, SW
Washington, D.C. 20202-4605
ስልክ ቁጥር፡-1-800-USA-LEARN (1-800-872-5327)

[7/20]